# ማስታወቂያ ለሰራተኞች

የስራ አጥነት ኢንሹራንስ (UI) ጥቅማጥቅሞች ስራ ለሌላቸው እና የቨርጂኒያ UI የብቃት መመዘኛዎችን ለሚያሟሉ ሠራተኞች ይሰጣል። የስራ ቅጥርዎ ካለቀ በኋላ ወይም የስራ ሰዓቶችዎ ከተቀነሱብዎት በኋላ በመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ የUI የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

**እርስዎ የሚከተሉትን ከሆኑ ለስራ አጥነት ኢንሹራንስ ጥቅማጥቅሞች ማመልከት ይችላሉ፦**

- ሙሉ በሙሉ ስራ አጥ ከሆኑ።
- በተቀነሱ ክፍያዎች ወይም የተቀነሱ ሰዓታትን እየሰሩ ከሆነ።

**የሚከተሉትን ማቅረብ ያስፈልግዎታል፦**

- የእርስዎን ሙሉ ሕጋዊ ስም
- የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥርዎን
- የመስራት ፍቃድዎን (የዩኤስ ዜጋ ካልሆኑ ወይም ነዋሪ ካልሆኑ)

**ሙሉ በሙሉ ስራ አጥ ከሆኑ፣ በጊዜያዊነት ከስራ ሲባረሩ፣ ወይም የተቀነሱ ሰዓታትን የሚሰሩ ከሆነ፦**

በመጀመሪያ የስራ አጥነትዎ ሳምንት ለስራ ይመዝገቡ እና ለጥቅማጥቅሞች የይገባኛል ጥያቄዎትን ያቅርቡ። የይገባኛል ጥያቄዎትን በኦንላይን በ www.vec.virginia.gov ወይም በደንበኞቻችንን የግንኙነት ማዕከል በ 1-866-832-2363 በመደወል ማቅረብ ይችላሉ። ለስራ በኦንላይን እዚህ ላይ ይመዝገቡ www.vawc.virginia.gov።

**ለጥቅማጥቅሞች ብቁ ለመሆን ህጉ የሚከተሉትን ይጠይቅዎታል፦**

- በቨርጂኒያ የቅጥር ኮሚሽን የይገባኛል ጥያቄ እንዲያስገቡ።
- ለቨርጂኒያ የስራ አጥነት ማካካሻ ህግ ተገዢ ከሆኑ ቀጣሪዎች ወይም በመነሻ ጊዜዎ (Base Period) ውስጥ ከማንኛውም ሌላ ስቴት በቂ ክፍያዎችን ያገኙ መሆንዎን።
- ከራስዎ ከመጣ ጥፋት ምክንያት ውጭ ስራ አጥ የሆኑ መሆንዎን።
- ስራ መስራት መቻል፣ ለስራ መገኘት እና ስራን በንቃት መፈለግ ያለብዎት መሆንዎን።
- የቨርጂኒያ የቅጥር ኮሚሽን ባዘዘው መሰረት ሪፖርት ማድረግዎን የሚቀጥሉ መሆንዎን።

የይገባኛል ጥያቄዎትን እስካላቀረቡ እና ሁሉንም የብቁነት መስፈርቶች እስካላሟሉ ድረስ የስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞችን ሊከፈሉ አይችሉም። ልክ ስራ አጥ እንደሆኑ ወይም ሰዓቶችዎ እንደተቀነሱብዎት የይገባኛል ጥያቄዎትን ማቅረብ ይኖርብዎታል። በቨርጂኒያ የስራ አጥነት ማካካሻ ህግ መሰረት ስላሉት መብቶች እና ግዴታዎች ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ይህን ድህረ ገጽ ይጎብኙ www.vec.virginia.gov ወይም በ 1-866-832-2363 ወደ የደንበኞቻችን የግንኙነት ማእከል ይደውሉ።

**ህጉ አሰሪዎች ይህንን ማስታወቂያ ለሁሉም ሰራተኞች በሚታይ ቦታ እንዲለጥፉ ይጠይቃል።**

**አሰሪዎችም የዚህን ማስታወቂያ ግልባጭ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ከስራ በሚለዩበት ጊዜ መስጠት አለባቸው (42 USC, §1103 (h)(2)).**

የእኩል እድል አሰሪ/ፕሮግራም
የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦች በሚጠይቁበት ጊዜ አጋዥ መሳሪያዎችን እና አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ ። እባክዎን ለቋንቋ ተደራሽነት/እርዳታ ወደ 866-832-2363 ይደውሉ ወይም በ፡- translation@vec.virginia.gov በኢሜል ይላኩ።

ይህ ማስታወቂያ በስፓኒሽ ይገኛል።
ቀጥተኛ ጥያቄዎች ወደ፦ **የአሰሪ መለያዎች**
**ፖ.ሳ. ቁ 26441**
**Richmond, VA 23261-6441**